**የመንግሥት ዕዳ ደንብን በተመለከተ አዳዲስ አስፈላጊ ለውጦች አሉ። ቤተሰቦችዎን በተረጋጋና ጤንነታቸው በተጠበቀ ሁኔታ ማቆየት እንዲችሉ ትክክለኛው መረጃ እንዲኖርዎት እንፈልጋለን።** ጎረቤቶቻችን በሙሉ ጤናማ ማህበረሰብን የሚደግፉ ወሳኝ መርሃ ግብሮች ውስጥ መሳተፍ ሲችሉ ይበልጥ ጠንካራ ኮሎራዶ ይኖረናል።

## የመንግሥት ዕዳ ምንድነው?

አንዳንድ ሰዎች ለግሪን ካርድ (ሕጋዊ ቋሚ ኗሪ) ወይም አሜሪካ ለመግቢያ ቪዛ ማመልከቻ ሲያስገቡ የመንግሥት ዕዳ ፈተና ማለፍ አለባቸው። ፈተናው ወደፊት አንድ ሰው የመንግሥት አገልግሎቶች የመጠቀም አዝማሚያው ምን እንደሚመስል ያመዛዝናል። የኢሚግሬሽን ባለሥልጣናት ይህን ግምገማ ሲያደርጉ የግለሰቡን ሙሉ የግል ሁኔታዎች፥ ዕድሜን፥ ገቢን፥ ጤናን፥ ትምህርት/ችሎታንና የስፖንሰራቸውን ቃል ወይም ውል ሁሉ ይመለከታሉ። አንድ ሰው ከዚህ በፊት የተወሰኑ የመንግሥት መርሃ ግብሮችን ተጠቅሞ እንደነበረም ከግምት ውስጥ ሊያስገቡ ይችላሉ።

## በቅርቡ የተለወጠው ምንደነው?

የመንግሥት ዕዳ ደንብ ለብዙ ዓመታት በሥራ ላይ ውሏል ሆኖም በ2019 ዓ.ም. ደንቡ ተጨማሪ የጥቅማጥቅም መርሃ ግብሮችን ለማካተት ተስፋፍቶ ነበር። ሆኖም በፌዴራል ፍርድ ቤት ውስጥ በቅርቡ በተከሰቱ ለውጦችና በአዲሱ ፌዴራል አስተዳደር በተወሰዱ እርምጃዎች ምክንያት ከአሁን ጀምሮ መንግሥት የ2019 ዓ.ም. የመንግሥት ዕዳ ደንብን በሥራ ላይ አያውልም። በብሔራዊ ደረጃ በተከሰቱት በእነዚህ አዲስ ለውጦች ምክንያት ደንቡ በ1999 ዓ.ም. ወደነበረው በስፋቱ በጣም ውስን ወደነበረው አቋሙ ተመልሷል።

## የመንግሥት ዕዳ ፈተና ውስጥ የተካተቱት የሕዝብ ጥቅማጥቅም መርሃ ግብሮች የትኞቹ ናቸው?

| የተካተቱ መርሃ ግብሮች* | ያልተካተቱ መርሃ ግብሮች |
| --- | --- |
| 1. የጥሬ ገንዘብ እርዳታ መርሃ ግብሮች (SSI፥ Colorado Works/TANF (ኮሎራዶ ወርክስ/ታንፍ)፥ OAP (Old Age Pension (የአዛውንት ጡረታ))፥ AND (Aid to the Needy Disabled (ለአካል ጉዳተኛ ችግረኞች እርዳታ))<br>2. በተቋም ውስጥ የረጅም ጊዜ እንክብካቤ የሚሰጡ የመንግሥት ገንዘብ ድጋፍ የሚያገኙ መርሃ ግብሮች | 1. Supplemental Nutrition Assistance Program (ተጨማሪ የምግብ እርዳታ መርሃ ግብር) (SNAP (ስናፕ)፥ Food Assistance (የምግብ እርዳታ)፥ ወይም Food Stamps (ፉድ ስታምፕ))<br>2. Federal Public Housing (የፌዴራል መንግሥት መኖሪያ) እና የመኖሪያ ቤት ኩፖኖች (ሴክሽን 8/Housing Choice Vouchers (የመኖሪያ ቤት ምርጫ ኩፖኖች) እና Continuum of Care (ቀጣይ እንክብካቤ))<br>3. Medicaid/Health First Colorado (ሜዲኬድ/ሄልዝ ፈርስት ኮሎራዶ)<br>4. Emergency Medicaid (ድንገተኛ ሜዲኬድ)<br>5. WIC<br>6. CHIP እና CHP+<br>7. የትምህርት ቤት ቁርስና ምሳ<br>8. የቤት ፍጆታ እርዳታ (LEAP)<br>9. የግብር ክሬዲቶች (እንደ EITC የመሳሰሉ)<br>10. CCCAP<br>11. ሌሎች የጥቅማጥቅም መርሃ ግብሮች በሙሉ |

"የተካተቱ መርሃ ግብሮች" ማለት በመንግሥት ዕዳ ፈተና ላይ ከግምት ውስጥ የሚገቡ የመንግሥት መርሃ ግብሮችን የሚመለከት ሲሆን፥ ለአንዳንድ ግለሰቦች በአንዳንድ ኢሚግሬሽን ሂደቶች ወቅት ሌሎች ሁኔታዎችን ለምሳሌ ገቢን ያካትታል። "ያልተካተቱ መርሃ ግብሮች" ከግምት ውስጥ አይገቡም።

## የመንግሥት ዕዳ ደንብ ማንን ነው የሚመለከተው?

**የመንግሥት ዕዳ ደንብ ለውጡ ሁሉንም ስደተኞች አይመለከትም።**

| | |
|---|---|
| **የአሜሪካ ዜጎች** | የመንግሥት ዕዳ እናንተን **አይመለከትም**። |
| **ሕጋዊ ቋሚ ኗሪዎች/ባለ ግሪን ካርዶች** | የመንግሥት ዕዳ እናንተን **አይመለከትም**። የዜግነት ማመልከቻዎች ላይ ወይም ግሪን ካርድ እድሳቶች ላይ **ተጽዕኖ አይኖረውም**። (ሆኖም አሜሪካን ከ180 ቀናት በላይ ለቅቀው የመሄድ ዕቅድ ካልዎት ሕጋዊ ባለሙያን ያማክሩ።) |
| **Temporary Protected Status (TPS) (ጊዜያዊ የተጠበቀ ሁኔታ) ያላቸው ግለሰቦች፥ U ወይም T ቪዛ ያላቸው፥ አሳይለም፥ ሬፍዩጂ ወይም ሌሎች ለሬፍዩጂ ብቃት ያላቸው ግለሰቦች ወይም Special Immigrant Juvenile Status (ልዩ ስደተኛ ልጅ ሁኔታ) እንዲሁም ሌሎች ለእነዚህ ማመልከቻ የሚያስገቡ ግለሰቦች** | የመንግሥት ዕዳ እናንተን **አይመለከትም**። |
| **ከአሜሪካ ውስጥ ሆነው የግሪን ካርድ ወይም የቪዛ ማመልከቻ የማስገባት ዕቅድ ያላቸው ግለሰቦች** | የመንግሥት ዕዳ እናንተን ሊመለከት **ይችላል**። በማመልከቻው ላይ ከግምት ውስጥ የሚገቡት በጣም ውስን የሆኑ የመንግሥት መርሃ ግብሮች (ከላይ የተዘረዘሩት) እንዲሁም ሌሎች ጉዳዮች ለምሳሌ ገቢ ናቸው። |
| **ከአሜሪካ ውጪ ሆነው የግሪን ካርድ ወይም የቪዛ ማመልከቻ የማስገባት ዕቅድ ያላቸው ግለሰቦች** | የመንግሥት ዕዳ እናንተን ሊመለከት **ይችላል**። ውሳኔ ከመወሰንዎት በፊት ከባለሙያ ጋር ይነጋገሩ። |

## ሌላ ምን ማወቅ ያስፈልገኛል?

- **አብዛኞቹ የመንግሥት ዕዳ ተጠቃሚ ስደተኞች በፈተናው ውስጥ የሚቆጠሩትን ጥቅማጥቅሞች የማግኘት ብቃት የላቸውም፥** አብዛኞቹ ጥቅማጥቅሞችም የመንግሥት ዕዳ ግምገማ ላይ ከግምት ውስጥ አይገቡም።
- በአሁኑ ወቅት ሥራ ላይ የዋለው ደንብ ከ1999 ዓ.ም. ጀምሮ በሥራ ላይ ውሎ የነበረው ሲሆን፥ ከ2019 ዓ.ም. ደንብ የበለጠ በጣም ውስን ነው።
- የኮቪድ-19 ክትባቶች አሁንም ሆነ ወደፊት ከመንግሥት ዕዳ አይቆጠሩም።
- የመንግሥት ዕዳ ደንብ ካሳሰብዎት እባክዎን ሕጋዊ ባለሙያን ወይም ታማኝ የማህበረሰብ ድርጅትን ያነጋግሩ። የቤተሰብዎ ደህንነትና ጤና ተጠብቆ እንዲቆይ እንፈልጋለን፥ መርሃ ግብሮቻችንም ይህንን ማድረግ እንዲችሉ ሊረዱዎት ይችላሉ።